## ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

### አርበኛው ይዞት የተነሳው ዓላማ የሚሸጥና የሚለወጥ አይሆንም።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ከፋኝ ብሎ የተነሳው አመፅ በግዜው የነበረው አስከፊ የደርግ ስርአትና የዛሬውን ወያኔ፤ ስልጣን ከመድረሳቸው በፊት ሲታለም ቆይቶአል። በዘመነ ወያኔ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ጢሰኛ እንዲሆ በመገደዱ ፤የከፋኝ ትግል በማደግና ወደ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በመሸጋገር ከፍተኛ መስዋእት ከፍሏል።አሁንም በመክፈል ላይ ይገኛል።

አርበኛው በየትኛውም የኢትዮጵያ በሕቡ፤የሚንቀሳቀስ  አሰመላሽ ክፈለ ጦር በማደራጀት በጠላት፤ ወያኔ ላይ የሚያደርሰው ጥቃት ራሱ የወያኔው አመራር ሳይደብቅ በተለያዩ ጊዜአት የወጡ መግለጫዎች ሁሉ የዘገቡት መሆኑ ሕዝባችን ጠንቅቆ ያውቃል። ይሁንና አርበኛው እስካሁን ድረስ በሕባችን ዘንድ ድጋፍ እንዳያገኝ ተደረገበት ዋነኛ ምክንያት በውጭ አገር የሚኖሩ አንዳንዶች፤ የአርበኛው ወገን ነን ባዮች፤ እኛ እንመራዋለን፤ እኛ እናወቅአለን በማለትና፤ በአርበኛው ስም ለሚነግዱት፤ ሕዝባችን በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው አድርጎታል።

አሁን ደግሞ አርበኛው ከግንቦት 7 (ሰባት) ጋር ተዋሐደ፤ የሚል የሐሰት ፕሮፖጋንዳ በመንዛት ላይ ይገኛሉ። ይህ አይነት ውሸት የመጀመሪያ ጊዜቸው ባይሆንም፤ የግንቦት 7 ጦር መንዝ ደረሰ፤ ከትግራይ ጦር ጋር ተባበርን፤ ከኤፍዲ ጋር ተባበረን፤ ከኦነግ ጦር አብረን ልንሰራ ነው፤ እያሉ የብዙ አገር ወዳድ ወገናችንን ኪስ ሲያራቁቱ ይታያሉ።

ለመሆኑ ግንቦት 7(ሰባት)ን እንደ ድርጅት ከመዉሰዳችን በፊት፤ኢትዮጵያ በወያኔ ቀንበር በወደቀችበት ግዜ፤ችግሩን ሁሉ እነማን ጠነሰሱት መሪወቻቸውስ እነማን ናቸው ብለን ብንጠይቅ የተሻለ መልስ ማግኘት ይቻላል። እንዲሁም ከነበረከት ስምኦን ጋር የደስደስ በውስኪ ሲራጩ፤ ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች ያለምን ስህተት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሲባረሩ፤ አኛ እነተካቸዋለን ብለው የተነሱ፤ ግማሾቹም እስከ አዲስ አበባ ከነንቲባነት ሲያገለግሉ የቆዩ፤ የወያኔ የፖለቲካ አማካሪወች የነበሩ ናቸው። በዚሁም አይነት ቅንጅት በተባለው የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ራሳቸው ደባ ሲፈጽሙና ሕዝቡን ለቆረጠ ሀገር አቀፍ ጠረ ወያዬ ክተት ሲነሳ፤ ትግሉን ሲያደናቅፉ የነበሩ ናቸው። ይህን ጸረ አገርና ሕዝብ የሆነ ሐይል፤ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር

እንኳንስ ሊዋሃድና ግንቦቶችን አጥብቆ የሚቃወምና የሚፋለማቸው መሆኑን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ እንዲገነዘብልን እናሳስባለን።

በመግቢችን እንደጠቀስነው፤ አርበኛው ይዞት ዓላማ የሚሸጥ፤የሚለወጥ አይደለም። ወደፊትም ሕዝባችን ይህንን ሰራዊት በቅርብ እየተመለከተ በምክር፤ በፋይናንስ፤የሞራል ድጋፍ በመስጠት ለምንፈልገው የሕዝብ ድል እንድንደርስ ይሁን።

ኣትዮጵያ ለዘላለም ትኑር፡

ሜ/ጀ መስከረም አታላይ
የአርበኞች ግንባር ሊቀ መንበር እና
የአስመላሽ ክፍለ ጦር አዛዥ